**በተሻሻለው የዘመን ኢንሹራንስ አ.ማ ላይ የተደረጉ ረቂቅ የመመስረቻ ፅሑፍ ለውጦችን በተመለከተ የቀረበ ማብራሪያ**

1. **መግቢያ**

   አሁን በስራ ላይ ያለው የኩባንያው የመመስረቻ ፅሑፍ በኩባንያው ባለአክሲዮኖች ፀድቆ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ፅ/ቤት ጥቅምት 03 ቀን 2016 ዓ.ም መመዝገቡ ይታወሳል፡፡ ይህ ሰነድ ከፀደቀ በኋላ በመመስረቻ ፅሑፉ ውስጥ በአፃፃፍ ግድፈት ከተጓደሉ ቃላቶች እና በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ መመሪያዎች መነሻ በማድረግ ማሻሻያ ማድረግ በማስፈለጉ ይህን በመመስረቻ ፅሑፍ ውስጥ የተደረጉትን ማሻሻያዎች የኩባንያው ባለአክሲዮኖች 5ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲያፀድቀው እንጠይቃለን፡፡

2. **የማህበሩን የመመስረቻ ፅሑፍ በድጋሚ ማሻሻል ለምን አስፈለገ?**
   - አሁን በስራ ላይ ያለውን የመመስረቻ ፅሑፍ በሰነዶቹ ላይ ያሉትን መሰረታዊ ሀሳብ በጠበቀ መልኩ በደፈናው የተቀመጡትን ለማብራራትና በዝርዝር ለማስቀመጥ እና በተገቢው ህግ እና አንቀፅ ለመደገፍ፤
   - ከኩባንያው የማኔጅመንት አባላት ጋር በመመካከርና በስራ ሂደት ያጋጠማቸውን ችግሮች በመለየት እና ለሥራው ጠቃሚ የሆኑ ሀሳቦችን በመመስረቻ ፅሑፍ ውስጥ እንዲካተት ለማድረግ ነው፡፡

3. **<u>በማህበሩ መመስረቻ ፅሑፍ ላይ የተደረጉ ዋና ዋና ለውጦች ፤</u>**

4. በነባሩ የመመስረቻ ጽሁፍ አንቀፅ 6( 3) ማንኛውም ሰው ባለአክሲዮን ሆኖ ለመመዝገብ ቢያንስ 10 አክሲዮኖች መፈረም ይኖርበታል፡፡ በሚለው አንቀፅ እና በአንቀፅ 8 (4) ላይ አንድ ባለአክሲዮን ከ5 በታች የሆኑትን አክሲዮኖች ነባር ላልሆነ ሰው በፍ/ቤት ትዕዛዝ ካልሆነ በስተቀር ሊያስተላልፍ አይችልም ፡፡በሚለው አንቀፅ መካከል ዝቅተኛው አክሲዮን 10 በሆነበት አግባብ በሁለተኛው አንቀፅ ላይ 5 አክሲዮኖችን እንደ መለኪያ መቁጠሩ ከ6-9 አክሲዮኖችን ማስተላለፍ ይችላል የሚል መልዕክትን የሚሰጥ በመሆኑ በአንቀፅ 8 ንዑስ አንቀፅ 4 ላይ ያለውን ከአንቀፅ 6 ንዑስ 3 ጋር በሚስማማ መልኩ በዚህ አግባብ ማስተካከል በማስፈለጉ፡- በአንቀፅ 8 ንዑስ ቁጥር 4 አንድ ባለአክሲዮን ከአምስት በታች አክሲዮኖች በሚለው ምትክ ከ አስር በታች አክሲዮኖች በሚል ማሻሻያ ቢደረግበት እና አንቀፁ እንደሚከተለው ቢነበብ **፡- አንቀጽ 8 (4)** አንድ ባለአክሲዮን **<u>ከአስር በታች</u>** አክሲዮኖችን ነባር ባለአክሲዮን ላልሆነ ሰው በፍ/ቤት ትዕዛዝ ካልሆነ በስተቀር በሽያጭም ሆነ በስጦታ ማስተላለፍ አይችልም፡፡

5. **አንቀፅ 10 (3)** ላይ እንዳለ የሚሰፍር ሆኖ በአፃፃፍ ግድፈት ላልተከፈለ ገንዘብ ለሚለው ገና ላልተከፈለ መባል ስላለበት በአንቀፁ ላይ ገና የሚል ቃል እንዲገባ ሆኖ እንደዚህ ቢነበብ፡- **ማናቸውም ለመግዛት የፈረመ ሰው ወይም ባለአክስዮን የሆነ ሰው የራሱ የሆነውን አክስዮን ያስተላለፈ እንደሆነ ካስተላለፈበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላ <u>ገና</u> ላልተከፈለው ገንዘብ ኃላፊነት የለበትም፡፡**

6. **አንቀፅ 16 (1)** በአንቀጹ ውስጥ የተፃፋ "ጉባኤው" የሚለው ቃል ከሙሉ አንቀፁ ጋር ሲነበብ የትርጉም ልዩነት የሚያመጣ በመሆኑ ጉባኤው *የሚለው ቃል "ጉባኤው**ን**" በሚል ቃል "ን" ተጨምሮበት ቢስተካከል እና እንደዚህ ቢነበብ፡- የጠቅላላ ጉባኤዎችን አጀንዳዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት ያለበት ጉባኤው**ን** የጠራው አካል ነው። ማለትም ትርጉሙ ጉባኤው የጠራው ሳይሆን ጉባኤውን የጠራው (ቅድመ ጉባኤ) ጉባኤው ከመጠራቱ በፊት አጀንዳው በቦርድ ዳይሬክተር የሚያዝ በመሆኑ፤*
7. **ነባሩ አንቀፅ 21 ስለ ጥቅም ግጭት** በንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 ላይ የባለአክሲዮኖች እና የዳይሬክተሮችን የግል እና የሶስተኛ ወገን ከማህበሩ ጋር የጥቅም ግጭት ሲኖር ድምፅ የመስጠት መብት የሚነፍግ ሲሆን ከዚህ በመቀጠል ያለው ንዑስ አንቀፅ 3 ለምልዓተ ጉባኤው መሟላት ግን ከቁጥር ውስጥ ይገባሉ በሚለው ላይ ይህ ንኡስ አንቀፅ የሚያወራው ከላይ በተመሳሳይ አንቀፅ ውስጥ ስላሉት ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 ስለሆነ በአንቀፅ 21 (3) ላይ "በዚህ አንቀፅ ውስጥ ............. የሚለው ሀሳብ **በአዲስ አንቀፅ 21 (3)** "በዚህ አንቀፅ **ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2**"የሚል ተካትቶበት እንደሚከተለው ተሻሽሎ ቢነበብ ፡-

**ምልዓተ ጉባኤ በሚሰላበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ 1 እና 2 ድምጽ የመስጠት መብት የተከለከሉ አክሲዮኖች ከቁጥር ውስጥ ይገባሉ።**

8. **ነባሩ አንቀፅ 21 (4)** "በዚህ አንቀፅ በንዕስ አንቀፆች 1-3 የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው በባለአክሲዮኖች ጉባኤ ላይ ድምፅ በመስጠት መብት በነፃ መጠቀምን የሚቀንስ ማናቸውም ድንጋጌ አይፀናም ።"በሚለው ላይ በመጀመሪያ ደረጃ ከላይ ያሉት ንዑስ አንቀፆች በራሳቸው የመመስረቻው አካል በመሆናቸው እንዲሁም በአንቀፁ ውስጥ በነፃ በሚል የተቀመጠው ቃል አፃፃፍ ግድፈት ስላለበት እና በህግም በአስገዳጅነት የሚገደብ መብት ካለም ለእነሱም እውቅና ከመስጠት አንፃር ሙሉ አንቀፁ እንደሚከተለው ቢስተካከል፡-አንቀፅ 21 (4) **"በዚህ መመስረቻ ጽሑፍ፤ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ እንዲሁም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚጣሉ ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው በባለክሲዮኖች ጉባኤ ድምጽ በነፃነት የመስጠት የባለአክሲዮኖች መብት አይገደብም።"**
9. **ነባሩ አንቀፅ 22** ስለ ዳይሬክተሮች ቦርድ በሚደነግገው ላይ ንዑስ አንቀፅ 22 (7) "ስለ ዳይሬክተሮች ቦርድ የአገልግሎት ክፍያ የብሄራዊ ባንክ መመሪያ የአገልግሎት ክፍያውን ገድቦት ሳለ እና ይህም በአንቀፁ ተጠቅሶ እያለ በድጋሚ የአገልግሎት ክፍያው ለባለአክሲዮኖች ከሚከፈለው የተጣራ ትርፍ 10% (አስር በመቶ) ሊበልጥ አይችልም" መባሉ የመቶኛ ስሌት ሊቀያየር የሚችል ከመሆኑ አንጻር እና በአንቀጹ ላይም የብሄራዊ ባንክ መመሪያ ገደብ መከበር ያለበት መሆኑ እስከተጠቀሰ ድረስ ፡- **አዲሱ 22 (7) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መምሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ለእያንዳንዱ ዳይሬክተር የሚከፈለው ማናቸውም የአገልግሎት ክፍያ ወይም ጥቅም በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ይወሰናል።** ቢባል

10. **በአንቀፅ 23 ንዑስ ቁጥር 3.20** የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣን እና ተግባራት በሚለው አንቀፅ ውስጥ ቦርዱ የማህበሩን ሂሳብ ከዋና ሥራ አስኪያጅ እና ከሚመለከታቸው ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች ፈራሚዎች ጋር በመሆን በጋራ ያንቀሳቅሳሉ። የሚለው አንቀፅ ከአሰራር አንፃር አጠቃላይ ቦርዱ ሳይሆን የቦርድ ሰብሳቢው በመሆኑ ሊያስፈፅም የሚችለው ይህ አንቀፅ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ስልጣን እና ተግባር በሚለው አንቀፅ 26 ውስጥ ቢካተት እና አንቀፅ 26 ከ1-6 የያዘ ሲሆን በሚሻሻለው መሰረት አንቀፁ ንዑስ አንቀፅ 7 ድረስ ኖሮት በ**26 (7) የማህበሩን ሂሳብ ከዋና ስራ አስኪያጅ እና ከሚመለከታቸው ፈራሚ የሥራ ኃላፊዎች ጋር በመሆን ያንቀሳቅሳል። ተብሎ ቢካተት**
11. **አንቀፅ 23 3.21** "የማህበሩን ሂሳብ የሚያንቀሳቅስ የቦርድ አባል ይወክላል።" የሚለው የዳይሬክተሮችን ቦርድ ስልጣን እና ተግባራት የሚገልፀው ንዑስ አንቀፁ ቦርዱ የማህበሩን የዕለት ተዕለት የስራ እንቅስቃሴ ለሚመራው የማህበሩ ዋና ስራ አስፈፃሚ በተጨማሪነት መወከል የሚኖርበት በመሆኑ ንዑስ አንቀፁ በዚህ መልኩ ማሻሻያ ቢደረግበት **"የማህበሩን ሂሳብ የሚያንቀሳቅስ የቦርድ አባል ወይም ዋና ስራ አስፈፃሚን ይወክላል።"**በሚል ተስተካክሎ እንዲጸድቅ፤
12. ነባሩ አንቀፅ 27 የዋና ስራ አስፈፃሚ ስልጣን እና ተግባር በሚዘረዝረው ንዑስ አንቀፆች በተራ ቁጥር 2. 2.3 **"የማህበሩን የሚንቀሳቀሱ ሀብቶች ይሸጣል…."** የሚለው የሚንቀሳቀሱ ብቻን የሚጠቅስ በመሆኑ **የማይንቀሳቀሱ** ሀብቶችንም የሚለው ተካትቶበት **ንኡስ አንቀፁ የማህበሩን የሚንቀሳቀሱ እና <u>የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች</u> ይሸጣል ፤ይለውጣል፤ያስተላልፋል እነዚህን ህጋዊ ተግባራት ለመስፈፀም በማኅበሩ ስም የሚያከናውኑ ኃላፊዎች ወይስ ሰራተኞች ይወክላል ።" ተብሎ እንዲጸድቅ**
13. ነባሩ **አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ 2 (2.16)** የመጨረሻው መስመር ላይ **መያዣ** ለማለት **መያዝያ** የሚል በመሆኑ **"መያዝያ ያደርጋል" የሚለው ቃል "መያዣ ያደርጋል** "በሚል የአፃፃፍ ግድፈቱ ተሻሽሎ እንዲጸድቅ ቢደረግ
14. **ስለማህበሩ ሂሳቦች በአንቀፅ 31 ንዑስ አንቀፅ 1** ስለ ማህበሩ ሂሳቦች አያያዝ እና አመዘጋገብ ሥርዓት ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑትን የመድን ህግ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ መመሪያዎችን የሚጠቅስ ብቻ በመሆኑ እና አሁን ላይ የሂሳብ ስራው ዓለም አቀፍ በሆነው የሂሳብ አዘገጃጀት መርህም ተግባራዊ እየተደረገ ያለ በመሆኑ በአንቀፁ ላይ ይህ መርህም ቢካተት እና በዚህ መልኩ ቢሻሻል ፡- **አንቀፅ 31 (1**) በመድን ስራ አዋጅ ቁጥር 746/2004 እና የመድን ስራ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር 1163/2012፤ የኢትዮጵያ ንግድ ህግ **፤ሀገራችን በተቀበለችው የዓለም አቀፍ የሂሳብ አዘገጃጀት መርህ** እና በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ መመሪያዎች መሰረት የሂሳብና የመዛግብት አያያዝ በተመለከቱ ድንጋጌዎች መሰረት በማህበሩ ሂሳብ አያያዝና አመዘጋገብም ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

15. **መጠባበቂያ ሂሳብን ስለመያዝ አንቀፅ 34** ከ1-4 ንዑስ አንቀፆች ያሉት ሲሆን በተጨማሪነት የማህበሩን ካፒታል ከፍ ለማድረግ በሚታሰብበት ጊዜ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ባንክ ፍቃድና መመሪያን ጠቅሶ መጠባበቂያውን መቀነስ እንችል ዘንድ በአንቀፁ ላይ ንዑስ አንቀፅ 5 ጨምረን ማለትም **34 (5)** "ሆኖም የማህበሩን ዋና ገንዘብ/ካፒታል/ ከፍ ለማድረግ ዓላማ ሲባል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የቅነሳውን ዝርዝር ሁኔታዎች አስመልክቶ አስቀድሞ በሚሰጠው ፈቃድና መመሪያ መሰረት ብቻ የማህበሩን መጠባበቂያ ሒሳብ መቀነስ ይቻላል።"የሚል አንቀፅ እንዲካተት ተደርጓል።

በመሆኑም ጠቅላላ ጉባኤው ዘመን ኢንሹራንስ አ.ማ በዳይሬክተሮች ቦርድ የተዘጋጀውን የመመስረቻ ፅሑፍ ማሻሻያ የባለአክሲዮኖች 5ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በንግድ ህጉ አንቀፅ 401 (1) በተሰጠው ስልጣን መሠረት እንዲያፀድቀው የዳይሬክተሮች ቦርድ ጠቅላላ ጉባኤውን በማክበር እጠይቃለው።